# የማን መንግስት? የትግሬ? የአድዋ?የወያኔ? የኢትዮጵያ?

ዘዋለ ዳዊት

## መንደርደሪያ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ስልጣን ይዞ ያለውን መንግስት ማንነት በተመለከተ ጥርት ያለ ግንዛቤ አለ ለማለት አያስደፍርም:: ገዢውን ክፍል ወያኔ ከማለት ያለፈና የኃይል አሰላለፍን ገላጭ የሆነ ትንተና ሲቀርብ አልታየም:: አንዳንዶች የወያኔ አገዛዝ ራሱን ኢሕአዴግ ስለሚል ጠቀመም ጎዳም የኢትዮጵያ መንግስት ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ያለው አገዛዝ " ከላይ እስከታች" በትግሬዎች የተሞላ ነውና የትግሬ መንግስት ነው ይላሉ:: የትግራይ ሕዝብ ሳይሆን የአድዋ ምርጦች ናቸው የተጠቀሙ የሚሉ ደግሞ የለም የመለስ አገዛዝ ከአክሱምና ሽሬ ቀልቀል ያለበት የአድዋ መንግስት ነው ይላሉ:: በመሰረቱ የወያኔ ቡድን ህጋዊነት ያለው መንግስ ት ሳይሆን በሕዝብ ላይ የተጫነ አገዛዝ መሆኑን ማወቅ ቢገባም ከተጨባጩ ሁኔታ ሳይንሳዊ ትንተና አኳያ መንግስት ምንድነው ለሚለው በቅድሚያ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል ፡ጥያቄውን ከስሜትና ንዴት ባሻገር ከትግሉ ግብና ከሳንሳዊ መሰረት አንፃር ለማየትና ለመተን ተን መጣር አለብን:: ወያኔ በጊዜው በሌሎች ታጅቦ የአፄ ኃይለስላሴና የኮለኔል መንግስቱ "መንግስቶች" የአማራው መንግስት ናቸው/ነበሩ በማለት ይቀሰቅሱ ነበር:: ለቅስቀሳ አመቺ ነው--አያደክምም:: የአማራ ለማኝ ሳይቀር ፍርፋሪ ይደርሰዋልና /ተረፍ መረፍ/ ጨቋኝ ነው ይሉ ነበር ወያኔዎቸ ተብሏል:: ታዲያ ዛሬ እኛስ ለምን ትግሬ ነገሰ አንልም? አንድ የፓልቶክ ተቺ እንዳለው " ከመለስ እስከ ለማኙ " ትግሬ ነግሷል እንበል? የማን መንግስት የሚለው ጥያቄ በትክክል መልስ ማግኘቱ አስፈላጊ ነው:: የትግሉ ግብን በተመለከተ ዕምብርት ነው:: ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ከተሰጠ የትግል ስልትና ዘላቂ ግብም ምን እንደሚሆንና እንዴትስ ትግል መካሄድ እንዳለበት፤ ማን ላይ መካሄድ እንዳለበት ለሁሉ ግልፅ ይሆናል:: ለማንኛውም የፖለቲካ ውይይትን ከስሜታዊነት በማራቅና በይሆን ይሆናል ሳይሆን በህብረተሰቡ ተጨባጭ እውነታ ላይ መመስረት ያስፈልጋል::የነገሮችንም ትርጉምና ይዘታን ማወቅ ያሻል::አሉባልታና ግልብ ትንተና ፖለቲካ አይደለም:: ሀቅም ከሳይንሳዊ ትንተና ጋር የተያያዘች መሆኗ መታወቅ አለበት:: አንድ የጦር መሪ በንዴትና ብስጭት ውጊያ ሊመራ ከተነሳ ጦሩን ያስጎዳል:: በፖለቲካም መስክ ያው ነው::

## የማን መንግስት?

## 1. መንግስት ምን ማለት ነው?

ልዩ ልዩ የፖለቲካ ተንታኞች መንግስት ምን ማለት እንደሆነ አስረድተዋል:: ክርክሩም ዛሬ የቀጠለ ነው:: የአመለካከት ልዩነቶች ከፖለቲካ ርዕዮት ጋር የተያያዙ ናቸው:: ከታሪካዊ የመንግ ስት ምንጭና ምንነት ባሻገር ሚናውና ይዞታው ምንድነው በሚለው ልዩነት አለ :: መንግስት ለሁሉም ሕዝብ የቆመ ነው የሚሉ አሉ:: መንግስት ለተወሰነ መደብ ወይም መደቦች የቆመ ነው የሚሉ አሉ:: ልዩ ልዩ ትንተናዎችን ማንበቡና ማወቁ፤ማመዛዘኑ ደግሞ አስፈላጊ ነው:: በአሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ጥናት በስፋት መደረግ ያለበት ነው:: በዝርዝር ልዩ ልዩ ትንተናዎችን ማንበቡ ተገቢ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ለጋራ ግንዛቤ በመሰረታዊ ደረጃ አጠቃላይ በሆነው ገፅታ ለማየት እንሞክር::

- መንግስት በአንድ በተወሰነ ግዛት የበላይ ባለስልጣን ሆኖ፤ የጦር ሀይሉ፤ የቢሮክራሲ፤ ወዘተ አዛዥ ናዛዥ ሆነ የተሰየመ ሀይል ነው::
- የመንግስት ስራ በሙያተኛ ደረጃ መንግስት መሆን ነው::
- በመሰረቱ መንግስት የሚያስጠብቀው የተወሰነ ጥቅም አለ ::
- ሁሉንም ሕዝብ የሚጠቅምና በእኩል የሚንከባከብ መንግስት እስካዛሬ እውን የሆነበት ሀገር የለም:: ለብዙሃኑ የሚጠቅም መንግሥት ሕዝባዊ ነው ይባላል::
- ዴሞክራሲያዊ ነን በሚሉ ሀገሮችም ቢሆን መንግስት በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስጠብቀ ው ጥቅም የብዙሀኑን አይደለም:: የብዙሀኑን ማለትም እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ሀገሮች ውስጥ የሰርቶ አደሩንና የአርሶ አደሩን ሕዝብ ጥቅም የሚጠብቅ መንግስት ከመጣ የጥቂቶች በዝባዦችን ጥቅም ሊያስቀድም አይችልም:: በተገላቢጦሹ ለምሳሌ የአሜሪካ መንግስት የብዙሀን ጭቁን ጥቁሮችን ጥቅም ሲያስቀድም አለመታየቱ የሚያስገርም አይሆንም::

መንግስት በጥንት የነበረ አይደለም:: መንግስት ያልሆነ መስተዳድርም በብዙ ሀገሮች ታይቷ ል:: ዛሬም ቢሆን ሶማሊያ አለመንግስትም ለመካሄድ ሞክራለች:: ዋናው ጉዳይ ግን ማንኛው ም ህብረተሰብ በመደብ የተከፋፈለ በመሆኑ ማንኛውም መንግስት ከመደብ ይዘት ወይም ቅራኔ ነፃ ሆኖ ለመሄድ አይችልም:: አንዳንዶች ይህ የግራ ወይም ማርክሳዊ ቲዎሪ ይመስላቸ ዋል--ግን ይሳሳታሉ:: አንድ ህብረተሰብ አንድ ወጥ አለመሆኑ ሊካድ አይቻልም:: አርሶ አደር አለ ፤ላባደር አለ ፤ ከበርቴ አለ ፤ ንዑስ ከበርቴ አለ :: እያንዳንዳቸው የራሳቸው

መሰረት፣ጠባይ፣ ይዘትና ፍላጎት አላቸው:: የሁሉም ህብረተሰብ በመደብ መከፋፈል የሚካድ አይደለም:: ቦታቸው በቅድሚያና ሁሌም በኤኮኖሚ ስፍራቸው ነው የሚወሰነው:: ማለትም መሬትና የምርት መሳሪያዎች ባለቤት በመሆን ባለመሆን:: መደቦች ከምርት መሳሪያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ይገለፃሉ:: መሬትና የምርት መሳሪያዎችን በቁጥጥሩ ያስገባው የከበር ቴው መደብ ሲባል፣ ጉልበቱን ለከበርቴው ሽጦ የብዝበዛ ሰለባ የሚሆነው ደግሞ በላቡ አዳሪ ነውና ላብ አደር ይባላል:: በገጠሩም በአጠቃላይ አርሶ አደር የሚባል ስያሜ ቢገልፀውም ድሀ፣መካከለኛና ሀብታም አርሶ አደር በሚል መፈረጅም የተሻለ ይገልፀዋል:: ከከበርቴውና ላባደሩ መሀል ያለውም ንዑስ ከበርቴ ይባላል:: መንግስት በዋና መልኩ የምርት መሳሪያ ባለቤቶች ወይም የከበርቴዎች መንግስት/ መሳሪያ ሆኖ ይታያል:: ለማንኛውም መንግስት ሕዝባዊ እስካልሆነ ድረስ መለያው በአመዛኙ ሀይልና ጫና እንጂ ፍቅር አይደለም :: በአብላጫው በጭቃ ሹምና በታጠቀ ወታደር፣ በጨካኝ ግብር ሰብሳቢ፣ በህሊናና ርህራሄ ቢስ ከበርቴና በአረመኔ ባለስልጣን ይከሰታል::

ስለዚህም መንግስት ማለት በአንድ በተወሰነ የግዛት ክልል ወይም ሀገር የፖለቲካና ሌላም ሁሉ ስልጣንን ይዞ የሚገኝ ሀይል ነው::በመሆኑም የማን መንግስት ለማለት ስንነሳ የዚህን መንግስት መደባዊ ይዘት--ለማን ቆሚል ለማን ይጠቅማል የሚለውን--ማወቅ ተገቢ ነው:: መንግስት የተባለው ኃይል መደባዊ ይዘቱ እንዳለ ሆኖ በስልጣን ያለው መደብ/ እንበል ከበርቴው/ልዩ ልዩ ክፍሎች ለበላይነት ወይም ለጥቅም በሚያደርጉት ሽኩቻ የገለልተኛ ሚና ን በመጫወት የስርዐቱን ደህንነት ይጠብቃል::ለአንዱ ወገንም ሊወስን ይችላል:: ግን በወሳኝ የመደብ ፍልሚያ ወቅት ገለልተኛ አይሆንም--የሚያስጠብቀውን የመደብ ጥቅም ይከላከላል እንጂ:: የከበርቴው መደብ ጥቅሙን ለማስጠበቅና ዕድሜውን ለማራዘም የተያያዙ መሳሪያዎ ች አሉት:: እነሱም ማስገደጃና መደለያ ናቸው:: ማስገደጃው የጦር ኃይሉ፡ፖሊሱ፣ፍርድ ቤቱ፣ የስለላና አፈና መዋቅሩ፣እስር ቤቱ ሲሆኑ መደለያው ደግሞ ሽርፍራፊ ለውጦችን ማካሄድ፣ ለተወሰኑ መጥቀም፣ ቢሮክራሲውን ለሹመትና ደሞዝ መጠቀም፣ ተቃዋሚ የሆኑት ን በገንዘብ ጥቅም መግዛት፣ መንግስት ቀጣሪ ነውና ስራ በመቸር (መደለል)፣ሙስናን ማስፋፋ ት፣ወዘተ ናቸው:: ህብረተሰቡን መከፋፋል፣ ለታማኝ መጥቀም፣ ከስራ በማባረር መቅጣት ሁሉ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ናቸው:: በተፈራራቂ ሀይልንም ድለላንም ይጠቀማል:: ሆኖም ወሳኝ ፍልሚያ ከመጣ፣ ሁናቴው ካሰጋው፣ትግል ከተፋፋመ ገዢው ቡድን የሚጠቀም በት ዋናው የማስገደጃ አካሉን ነው:: የግንቦት-ሰኔን ጭፍጨፋ ያስታውሷል:: መረን በለቀቀ / ሌሴ ፌየር/ ካፒታሊዝም ስርዓት የመንግስት ሚና የከበርቴውን ጥቅም ማስጠበቅ ነው:: በሶሻሊስት ወይም ሶሻል ዴሞክራሲ ስርዓቶች ደግሞ መንግስት የሚቆመው ለተለየ መደብ ነውና በኤኮኖሚውም ጣልቃ ይገባል:: የገበያ ኤኮኖሚን መርህ በተቀበለበትም ቢሆን ሰው በላ ካፒታሊዝም ሕዝቡን ግጦ እንዳይጨርስ ገደብ ያበጃል፣ የሰርቶ አደሩን መብት ያስጠብ ቃል፣የሀገሪቷን ቁልፍ ተቋሞች በመንግስት ቁጥጥር ስር ያስገባል:: (መረን የለቀቀ ካፒታሊዝ

ም ዋናው ጠበቃው ሚቹ ፍሪየድማን ይል እንደነበረው ሳይሆን በሕዝብ መከራና ድቀት ላይ ተመስርቶ ለዴሞክራሲም ፀር ሆኖ እንደሚገኝ በዝርዝር ለመረዳት በቅርቡ የወጣውን የ ናኦሚ ክላይንን "ሾክ ዶክትሪን" መፅሀፍ ያንቡ)

2. <u>የመንግስት መደባዊ ይዘት እንዴት ይገለፃል?</u>

የአንድን መንግስት ማንነት ለማወቅ ለማን ቆሟል የሚለውን መርምሮ ማወቅ ያስፈልጋል። ያለው መዋቅር /የአፈናው፣ ህጉ ፣ቢሮክራሲው/ በተወሰነ የቀውጢ ሁኔታ የገዢ መደቦች ገላጋይ ወይም ገለልተኛ ሀይል መስሎ ቢታይም በመሰረቱ ይህ አገዛዝ ለማን ያገለግላል፣የማን ን ጥቅም ያስቀድማል ብሎ ማወቅ ተገቢ ነው። ይህን ለማወቅ ደግሞ በሀገሪቷ ያለውን የመደ ብ አሰላላፍ እስቀደሞ መመርመርና በወሳኝ ግብግብ ወቅት ብቻ ሳይሆን በቀን ተቀንና በአጠ ቃላዩ ያ መንግስት ለማን እንደቆመ ማጤን ያስፈልጋል። የመንግስት ማንነት የሚገለጠው በስልጣን ላይ ባሉት ግለሰቦች ማንነት ወይም ቀለምና ብሄረሰብ አይደለም። የፖለቲካ ስልጣ ን የያዙ  መስለው ከሚታዩት ባሻገር መንግስት እንደ ተቋም ታዛዥነቱ ለማን ነው? የማንን ጥቅም በቅድሚያና በዋናነት ያስከብራል? ብለን መጠየቅና ትክክለኛውን ምላሽ ለማግኘት መጣር አለብን። የኢትዮጵያ ዕድሜ ረጅም የነበረ ቢሆንም ዘመናዊ ማዕከላዊ መንግስት ምስረታን በተጠናከረ መልክ ፈር ሊያስይዙ የተነሱት አፄ ቴዎድሮስና ምኒሊክ ናቸው። የተጀመረውም የማዕካለዊ መንግስት ምስረታ በአፄ ኃይለስላሴ ተጠናቆ አንድ ንጉስና ማዕከላዊ መንግስት በዘመናዊ አስተዳደርና ማዕከላዊነት መልክ እውን ሆኗል። በፊውዳሉ ስርዓትም በልዩ ልዩ ቦታዎች ንጉስና ባለስልጣን የነበሩት  በማዕከላዊው ተጠቃለው በንጉሱ ስር ተጠቃሚና የስልጣን ተካፋይ በመሆናቸው ከአካባቢ ባሻገር ተመሳሳይና የጋራ ጥቅም ያለው የፊውዳል መደብ በሀይል ታጅቦ ሊዳብር ቻለ ። መንግስትም ዘመናዊ ይዘትን ሲተዋ ወቅ ደግሞ ለባዕድ አቀባይና ታዛዥ የሆነ አቀባባይ ከበርቴም ተወለደ ። ቢሮክራሲውም ሲስፋፋ በዚሁላይ የተመሰረተ መደብ ብቅ ማለቱ አልቀረም። በተበዳይ ደረጃ ያው ለጪሰኝነ ትና ለገባርነት የተዳረገው አርሶ አደርና ቁጥሩም ባይበዛም በዘመናዊ ፋብሪካዎችና ተቋሞች የሚሰራ ላባደርም ነበር። ተማሪ፣አስተማሪ፣ቢሮ ሰራተኛ፣ፀሀፊና ከተሜውም ከላይኛውና ታችኛዎች መደቦች መሀል በንዑስ ከበርቴነት ተፈርጆ ቆመ። ይህን ዓይነት በነበረው ህብረተ ሰባዊ ገፅታ የአፄው መንግስት የማንን ጥቅም ያስጠብቃል ብንል በቅድሚያ የፊውዳሉን መደ ብ ጥቅም መሆኑግልፅ ነበር። ይህ ገዢ መደብ ደግሞ አማራ ብቻ ሳይሆን ትግሬም፣ከኤርትራ ም፣ ከኦሮሞም ከአፋርም ወዘተ እንደነበር ታይቷል። የአፄ ኃይለስላሴ የሀገር ግንባታና አን ድነት ማጠናከሪያ ምርጫ የሀገሪቷ ቋንቋ አማርኛ እንዲሆን መግፋትን፣ ለኦርቶዶክስ ሀይማኖ ት መስፋፋት ቅድሚያ መስጠትን የተቀበለ ቢሆንም ያ መንግስት የአማራ መንግስት አልነበ ረም። የነበረውመንግስት ብሄረሰብ ሳይለይ በዝባዥ ከመሆኑና ብዙሃኑ የአማራ ሕዝብ ተበዝባ ዥ ሆኖ ከመቀጠሉ ሌላ በመንግስት በመጠቀምና በኤኮኖሚ ዕደገትም ደረጃ አማራው ሕዝ ብ ሲበደል የቆየነበር።ጠባብ ብሄረተኞችና ደጋፊዎቻቸው "አማራ ገዛ" የሚሉት መሰረተ ቢ

ስ ፕሮፓጋንዳ እንደነበር ጥርጥር የለውም፡፡ የአማራ መንግስት? አማራው ተጠቀመ? በለፀገ ? ጎጃምና ትግራይ፤ ኤርትራና ሸዋ/ከዋናው ከተማ ውጪ/ ቢነፃፃሩ ማን በነበረው መንግስት ይበልጥ ተጠቃሚ ነበረ ለሚለው መመለስ ይቻላል፡፡ በዚያን ወቅት በደቡብ ኢትዮጵያ የመሬት ቅሚያው ከብሄረሰብ ጭቆና ጋር ተቆራኝቶ የነበር ቢሆንም በትግራይ ግን የሰፈረ የውጭ ባላባት ካለመኖሩ ሌላ በትግራይ ላይ በሌላው ላይ የነበረው ብሄረሰብ ነክ በደል ወይም ንቀትደረሰ ለማለት የሚቻል አልነበረም፡፡ ዛሬ ነፍጠኛ ብሎ በአማራው ላይ የሚጮኸው ወያኔ የሚደብቀው አንድ ሀቅ ሌላውን ገባርና ጢሰኛ በማድረጉ ሂደት የአማራ ውም የትግሬውም የሌላውም ባላባት ወይም ፊውዳል የተሳተፈበት መሆኑን ነው፡፡የደርግም መንግስት ቢሆን ከልዩ ልዩ ብሄረሰቦች የተውጣጡ ባለስልጣኖች ያሉት መንግስት የነበረ ከመሆኑ ሌላ ለአንድብሄረሰብ ጥቅም የቆመ አልነበረም፡፡ የመንግስቱ ኃይለማርያምን መንግስ ትም የአማራ መንግስት ብሎ መሰየሙና መፈረጁ ስህተት ነበር፡፡ የባለስልጣኖቹ የብሄረሰብ ስብጥርም (ወያኔ ቢክደውም የታየ ነበርና) በግልባጩ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግስት አላደረገ ውም፡፡ የፖለቲካናየኤኮኖሚ ስልጣኑን ይጠቀም የነበረው ገዢ መደብ እንጂ የተወሰነ ብሄረሰ ብ አልነበረም፡፡ በእርግጥ በመንግስታዊ ካፒታሊዝም ስርዓት ገዢው መደብ ወዲያው ንጥር ብሎ ላይታይ ቢችልም የደርግ መንግስት ለላባደሩና አርሶ አደሩ ወይም በብሄረሰብ ደረጃ ለአንድ ወይም ሁለት ብሄረሰብ ጥቅም ያልቆመ እንደነበር ይዘቱንና ሂደቱን በመመርመር መረዳት እንችላላን፡፡

3. <u>የወያኔ መንግስት ለማን የቆመ ነው?</u>

ለዚህ ዕሁፋችንና ለትንተና ያመች ዘንድ ይህን አገዛዝ መንግስት እንበለውና ከመጀመሪያው ልዩ ይዘቱን በመመልከት እንነሳ፡፡

- ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ መነሻውና መድረሻው ብሄረሰቡን ማስቀደምና መጥቀም ነው፡ ከትግራይ ግንጠላ ዕቅድ ጀምሮ ስልጣን እስኪይዝም ቢሆን “ትግራይ ትቅደም” ብሎ የተነሳ ኃይል ነው፡፡
- ዕቅዱ በትግራይ የበላይነትም ስር ቢሆን ሀገር አንድነትን ማረጋገጥ ሳይሆን ሀገርን መከፋፈል፤ ማዳከምና መበዝበዝ ነው፡፡
- ይሁነኝ ብሎና አምኖበት የሚንቀሳቀስበት የፖለቲካ መርህ ጠባብ ብሄርተኛነት ነው፡
- የአገዛዙ መሰረት የሆነው ጦር ሀይል (ይህን ከአፄውም ከደርጉም ያነፃፅሯል) በአብላ ጫው ከራሱ ብሄረሰብ የተውጣጣ ነው፡፡
- የሚከተለውና ያመነበት ፖሊሲ ከራሱ ብሄረሰብ ውጪ ያለውን ሕዝብ በተለይ መጨቆንና መበደል ነው፡፡ አርባ ጉጉ፤ ምስራቅ ወለጋ፤ጋምቤላን፤አጋዴንን ወዘተን ይጠቅሷል፡፡

- *የጥቅም መተሳሰሪያው በቅድሚያ ብሄረሰባዊ አንድነት ነው:: መሰረቱን ለማስፋት ሲል በክልል ደረጃ --አሁንም ብብሄረሰብ መሰረት--አጃቢ ከበርቴውችንና ተጠቃሚ ዎችንም ፈልፍሏል::*

*ይህ እንዳለ ሆኖና ዋና ዋናዎቹ ወያኔዎች ከአድዋ ቢመጡም የአድዋ መንግስት ሊባል የሚችል አይደለም:: የወያኔ ይዘቱ አድዋዊ ሳይሆን ትግራዊ ነውና:: በውስጡ የአካባቢ ስሜትና ልዩነት ቢከሰትም/ በአሽአ ማለትም አድዋ ሽሬ አክሱም መጤዎችና በሌሎቹ መሀል/ መሰረቱ ትግራይ ወይም ትግራዊ ነው:: ያለው መንግስት ኢሕአዴግ በሚል ሽፋን ከሌሎች ብሄረሰብ የመጡትን ለስልጣን ቦታዎች ቢያበቃም ዋናውና ወሳኙ ስልጣን በወያኔ እጅ የተያዘ በመሆኑ መንግስቱን ህብረ ብሄራዊ ማለት አይቻልም:: በአፄውና በደርግ ጊዜ ሁለቱም መንግስታት የአማራ ተብለው በጠባቦች ቢፈረጁም እነዚህ መንግስታት ለአማራው በተለይ አለመጥቀማቸው ብቻ ሳይሆን አማራው ሕዝብ የእኔ ብሎ አልወሰዳቸውም--ታገላቸው እንጂ:: የወያኔን መንግስት በሚመለከት ግን አፍን ሞልቶ ይህን ማለት ባለመቻሉ የማን መንግስት የሚለውን ለመመለስ ችግር ፈጥሮ ይገኛል:: መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ ለትግራይ ሕዝብ የቆምን ነን ይላሉ:: ከኢትዮጵያዊነታች ን በፊት ትግራዊነታችን ሲሉም ተደምጠዋል:: የአማራው ሕዝብ የነቃው ክፍል የአፄውንም የደርጉንም መንግሰታት በመታገል ግንባር ቀደም ሚናን ሲጫወት ዛሬ የትግራይ ምሁራን በፀረ ወያኔው ትግል ያላቸውን ቦታና ሚና በባትሪም ተፈልጎ አለሁ የሚል አይደለም:: ባለፈው ግንቦት 97 የተከሰተው ማለትም በርካታ የትግራይ ተወላጆች ለቅንጅትም ለህብረቱም ድምፅ መስጠታቸው የሕዝብ ትግል ሲያይል የትግራይ ተወላጆችም ወደ ሕዝባዊው ጎራ መምጣታቸው አይቀሬነቱን ሲያመላክት በዚያው ጊዜ ደግሞ የመለስ ተቃዋሚ ነን ይሉ የነበሩት ደግሞ በስርዓ ቱ የመጣው በእኛም ላይ የመጣ ነው ብለው በመስጋት ወደ ወያኔ ጠጋ ማለታቸውም ታይቷል:: ከመለስ ተጣላን ብለው ግን አሁንም የትግራይ ጠባብ ብሄርተኝነት አቀንቃኝ የሆኑትን ና ራሳቸ ውን አሬና ያሉትንም ሆነ ሌሎችንም መመልከትም በቂ ነው::*

*ወደ መደባዊ ይዘት ስንመለስ ምንም እንኳን ይህ መንግስት መሰረቱ ብሄረሰባዊ ማንነቱ ቢሆንም ፤ ምንም እንኳን ለራሱ ክልልና ብሄረሰብ ማዳላቱ ግልፅ ቢሆንምና በትግራይ ተወላጆችም ዘንድ ጥርት ያለ አቅዋምና አሰላለፍ ባይታይም ይህን መንግስት የትግራይ ሕዝብ መንግስት ወይም በደፈናው የትግሬ መንግስት ማለቱ ትክክል አይሆንም:: ለምን ስንል መልሱ ግልፅ ነው::*

*1ኛ/ ብዙሃኑ የትግራይ ሕዝብ በዚህ መንግስት ተጠቃሚ አይደለም:: ወያኔ መሰረቱን ለማስፋት በክልሉ ተረፍ መረፍ--ትርፍራፊ-- ቢዘራም ዛሬም ቢሆን ብዙሃኑ የትግራይ ሕዝብ ታፍኖ የተያዘና የሚሰቃይ ድሀ ሕዝብ ነው:: በመቀሌ ይህ ያ መንገድ ተሰራ ወዘተ የሚባለውም በጣም ውሱን ክፈልን የሚጠቅም ሲሆን በሌሎች ቦታዎች የሚካሄዱት ግንባታዎች ደግሞ በአንፃሩ የወያኔን ሰፊነት ወይም ኢትዮጵያዊነት የሚያሳዩ አለመሆናቸውም መጠቀስ ያለበት ነው::*

2ኛ/ የሕዝብ መንግስት ለመባል ከውልደት ባሻገር ለዚያ ሕዝብ መቆምንና ዴሞክራሲ ማስፈንን የግድ ይላል። በትግራይ ዴሞክራሲ ደብዛዋ ጠፍቶ በወያኔ ካድሬዎች የሚበደል ሕዝብ ነው ያለው። ሕዝብ ስንል ደግሞ ካድሬና ንፁስ ከበርቴውን፤ የድርጅት አባሉንና እበላ ባዩን ሳይሆን ብዙሃኑን ነውና ብዙሃኑ የትግራይ ሕዝብ የወያኔ መንግስት ተጠቃሚ አይደለም። ወያኔ የትግራ ይን ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ለማጣላትና ለወደፊትም ግንጠላውም በትግራይ ድልዳል ለመስ ራት ቢጣጣርም ከሕዝብ አንፃር ዕቅዱም ተቀባይነት የለውም፤ግንባታውም ፋይዳ የለው ማለት ይቻላል።

*ታዲያ የወያኔ መንግስት የማን መንግስት ነው?*

ባልሆነው እንጀምር እንበልና፤

- *የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግስት አይደለ ም።*
- *የወያኔ መንግስት ህብረ ብሄራዊ መንግስት ሆኖ በመደብ ደረጃም የሚፈረጅ አይደለም። ለምን ቢባል ምንም እንኳን ከልዩ ልዩ ብሄረሰብ የመጡ የፖለቲካ ባለስልጣኖችና ከበርቴ ዎች ተዛንቀው ያሉ ቢሆንም በፖለቲካውም በኤኮኖሚውም መስክ የበላይነትንና ስልጣን ን የያዘው የወያኔ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን ነው። ስልጣን በትግራይ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን እጅ ናት። እያደገ የመጣው ና የመንግስት ስልጣንን ተጠቅሞ እየከበረ ያለውም የከበርቴ ቡድን በዋና ደረጃ ጠባብ ብሄረተኛው ወያኔ ነው። በእርግጥ ይህ ከበርቴ ቡድን መሰረቱን ለማስፋት ኬሌሎች ብሄረሰቦች ከበርቴዎችም ጋር ተቃቅፏል። በዓለም አቀፍ ደረጃም ከሀያሉ መንግስትና ከምዕራብ ኩባንያዎችና ተቋሞች (ዓለም አቀፍ ባንክ፤አይኤ ም ኤፍ ወዘተ) ጋርም ተያይዟል።*
- *ስለዚህም ያለው መንግስት የትግራይ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን ወይም ከበርቴ መንግስት ቢባል ትክክል ነው። የትግራይ መባሉ ትክክል የሚሆነውም በብሄረሰብ ደረጃ የተደራጀ፤የተመሰረተና የሚሰራም በመሆኑ ነው። ተለጣፊዎቹና አጃቢዎቹ በመሰረቱ ሚዛናቸው ቀላል ነው። ይህ መንግስት የቆመውና የሚከላከለው ዋና ጥቅም የትግራይ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድኑን ጥቅም ነው። ከወያኔ ልፈፋ ባሻገር የዚህ ቡድን ጥቅምና የትግራይ ሕዝብ ጥቅም ደግሞ ተወራራሽ ወይም አንድ አይደለም። ያለውን መንግስት የትግሬ መንግስት ማለቱ ከመሰረታዊ ትንተና አንፃር ትክክል ካለመሆኑ ሌላ ብዙሀኑን የትግራይ ሕዝብ ከወያኔ ጠባቦች ለይቶ ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ማሰለፉ ለትግላችን ድል ወሳኝ ነውና ያለው መንግስት የትግራይ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን/ከበርቴዎች መንግስት መሆኑን ማስረገጥ ተገቢ ነው።*

የዚህን ገዢ ቡድን ይዘት በሚገባ ያልተረዱ በዚህም በዚያም የተሳሳት አቅዋም ማንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የምዕራቡን ሊበራል ዴሞክራሲ አወዳሾች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ አሜሪካ ውስጥ እንዳለው የሲቪል መብት ንቅናቄ ተመሳሳይ እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ይሄውም አሜሪካ ውስጥ ያለው የሲቪል መብት ንቅናቄ የሚነሳው ስርዓቱ አነሰም በዛም ህጋዊ ተቋማት ስላሉት የሚደረግ ትግል ማህበራዊ ስርዓቱን ለመለወጥ ሳይሆን በሕገ መንግሥቱ ላይ የተደነገጉትን አንቀፆች (ቢል ኦፍ ራይትስ) ተግባራዊ እንዲሆኑና ብሎም በስርዓቱ ውስጥ ለመካተት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን ይህንን የሚያስችል አይደለም፡፡ ሕገ መንግሥት ለይስሙላ አለ ይባል እንጂ ህጋዊ መሰረት የሌለው የሕዝብን መብት ሙሉ በሙሉ የረገጠ ሆኖ እናገኘዋለን ከዚህ ስርዓት ጋር የሚደረገው ትግል በሕግ መንግሥቱ (ወያኔ) ውስጥ የተደነገጉት አንቀፆ ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግና በስርዓቱ ለመካተት/ለመታቀፍ አይደለም፡፡ ትግሉ የወያኔን ስርዓት በሌላ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመተካት ነው፡፡

ሊበራል ዴሞክራቶች ይህን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ስለተሳናቸው ወያኔን “ጠላት አትበሉ”፣ “ተቀናቃኝ ” በሉ፣ በወያኔ ስር የሚገኙትን የመንግስት ዋልታዎችን “ነፃ” ማድረግ ነው እንጂ ስልጣን ለመቀማት አትሞክሩ፣ ወያኔ “ስነ ልቦናዊ ለውጥ” እንዲያደርግና “ ዴሞክራሲያዊ” እንዲሆን እንታገላለን፣ የትግላችን ስልት “ሰላማዊ ብቻ” ነው ይላሉ፡፡ ይህን መሰል አቅዋም ቢገፉም በሕዝብ ተቀባይነትን በማጣቱ ውዥንብሩ ለራሳቸው ተርፏል፡፡ የፖለቲካ ክስረትም ዕጣቸው ሆኗል፡፡

ሌላው ቡድን ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ ከገዢው ቡድን የተባረረው ነው፡፡ የጉልቻ ለውጥ ወጥ የማያጣፍጥ መሆኑን ከማሳየት ባሻገር የመንግስትን መደባዊ ይዘት ከተረዳን የግለሰቦች ለውጥ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል ያሳያል፡፡ የዚህ ቡድን አቋምና ፍላጎት ስልጣን የያዘውን መለስን አባረው ራሳቸውን በቦታው ለመተካትና የወያኔን ስርዓት ማስቀጠል ነው፡፡ ምንም እንኳን በእዚህ ቡድንና በመለስ ቡድን መሀል ያለው ቅራኔ ለትግሉ መፋፋም ቢጠቅምም የቡድኑ መሰረታዊ ገፅታ ያው ጠባብ መሆኑን መሳት ይሆናል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በሕዝብ መሀል መሰረታዊ ቅራኔ ያለ አስመስሎ መውሰድ ስህተት ይሆናል፡፡ በወያኔ የ1967 ዓ.ም. ድምዳሜ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በአንድ በኩል በጋራ ቆመው ከአማራው ሕዝብ ጋር በማይታረቅ ቅራኔ የገቡ በመሆናቸው መፍትሄው ግንጠላ ነው ተብሎ ነበር፡፡ ይህ የጠባቦች ውዥንብር ዛሬም ነፍስ ዘርቶ መላ የትግራይን ሕዝብ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ብሎ ሊያስደመድም እያታገለ ነው፡፡ በብሄረሰብ ጥያቄ ዙሪያ ያለው ችግር የሚፈታው በዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፈንና የመደብ አንድነትን--አጋርነትን ባስቀደመ ሂደት መሆኑን የዘነጉ አልጠፉም፡፡ ወያኔ ክልል ብሎ የአካባቢ የጥቅም ተቋዳሾችን ቢፈለፍልም ራሰን ማስተዳደር የሚለው ባዶ ቃል መሆኑና አሁንም የጠባቡ ወያኔ በላይነት ሰፍኖ እንዳለም የሚታይ ነው፡፡ መሬት ለአራሹ ብቻ ሳይሆን የእኩልነትና መብት ጥያቄም ገና ምላሽ አላገኘም፡፡

የመንግስትና ስርዓት ለውጥ ማለት የጥገና ለውጥ ወይም ግለሰብን በሌላ መተካት ማለት አለመሆኑ መታወቅ አለበት። ሳይንሳዊ ትንተናና ግምገማን በስሜታዊ ድምጻሜ መተካት ከሰፊነ ግንዛቤያችን ጠቃሚም ትክክልም ሊሆን አይችልም። በየመድረኩ የሚነገረውና በተገኘው ዕድል ሁሉ የሚቀርበው ትንተና ሕዝብን በአንድነት ይዞ ቀና ግንዛቤን ሊሰጥ የሚችል ሳይሆን በተቃራኒው ያልተፈለገውን አስከትሎ ተፈለገም አልተፈለገም ለገዢው መደብ የሚጠቅም ከሆነ ጎጂ ነውና የማን መንግስት ለሚለው የምንሰጠው መልስ ትክክል መሆኑ ወሳኝ ነው። ለምሳሌ አንዳንዶች ከ 1983 ወዲህ መላ የትግራይን ሕዝብ በጠላትነት ፈርጅውና ትግላችን ፀረ ትግሬ ነው ብለው ሊነሱ መፈለጋቸውን አስደምጠዋል። አንድም የትግራይ ሕዝብ የስርዓቱ ተጠቃሚ ሆኗል ከሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ትግሌ ፀረ አማራ ነው ብሎ "በቀላሉ" ማሰባሰብ ስለቻለ ለትግላችን መደባዊ ይዘት ከመስጠት በፀረ ትግሬነት ደረጃ መወሰኑ ያዋጣል ከሚልም ነው። ይህ አቀዋም ራሱ ከንዴትና ብስጭት በተለይም የትግራይ ንዑስ ከበርቴና ምሁሮች ከጠባቡ ሀይል መቆራኘታቸውን በመመልከት የተነሳ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። (ወያኔም ሰርጎ ገቦቹን በጭፍን ፀረ ትግሬነት ተሰማሩ ብሎ እንደሚያሰማራም የሚታወቅ ነው) ። ይህ አቀዋም ማለትም መላ ሕዝብን በጠላትነት መፈረጁ ደፋር አቀዋም መያዝ የሚመስላቸውም አሉ። ማን ይፈራቸዋል፤ እናሳያቸው ዓይነት መሆኑ ነው። ይህ ግን ከባድ ስህተት ነው። ቀደም ብለን እንዳቀረብነው የትግራይ ሕዝብ በሞላ የወያኔ ስርዓት ተጠቃሚ ነው ማለት ስህተት ነው። የተጠቀመ ቢመስለው እንኳን ተሳስተሃልና ከቀሪው ሕዝብ ጎን መሰለፍ ይሻልሀል ብሎ መምከር ይመረጣል እንጂ ጠላት ነህ ብሎ ማግለሉ አያዋጣም። የትግራይ ሕዝብ የጋራ ትግላችን አካል መሆን ያለበትም ነውና በጠላትነት ፈርጀን ጠቅለን ለወያኔ ልንሰጠውና ወያኔን ልናጠናክረው አይገባም። በአጭሩ በዘዴም ሆነ በረጅም ዕቅድና የሕዝባዊ ትግል ይዘትና መሰረት አኳያ ሲታይ ይህ ሕዝብን በጅምላ በጠላት መፈረጅ ከባድ ሰህተት ከመሆኑ ሌላ ሲስተጋባም ጠቀሜታው ለወያኔ ብቻ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። አለበለዚያ ወያኔ በቀደደው የጠባብነት ቦይ መፍሰስና ለእርስ በርስ ዕልቂት አጋር መሆን ይከተላል።

## <u>ለማጠቃለል</u>

መንግስት መሰረቱ የሕዝብ ምርጫና ድጋፍ ባልሆነበትና የቆመው ለውሱን ከበርቴዎች ጥቅም ከሆነ አሉታዊ ሚናው ከፍ ያለና የጎላ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ለሰፊው ሕዝብ

ጥቅም የሚሰራ መንግስት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ ህብረተሰቡ በስርዓትና በሰላም ወደ ብልፅግ ና ይጓዝ ዘንድ መንግስት መኖሩ ባለንበት ወቅት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው መንግስት ለመመስረት መታገል ያስፈልጋል፡፡ ይህን በተመለከተ ሀገር ወዳድ ሀይሎች ተሰባስበው ዴሞክራሲያዊ የሽግግር መንግስት  በማቋቋም ሕዝብ በነፃ ምርጫ የሚፈልገውንና የሚበጀውን መንግስት እንዲያቋቅም ማድረግ አለባቸው፡፡ የሚመረጥም መንግስት የሕዝብን አደራ ሽሮ ወይም ዘንግቶ በሌላ ጎዳና የሚጓዝ ከሆነ ማውረጃውም መንገድ በህግ ተደንግጎ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ የሀገሪቷ ጦር ኃይልም ለህገ መንግስትና ለህዝብ ተገዢ መሆን አለበት እንጂ  ለተመረጠ ፓርቲ ወይም ድርጅት ታዛዥ መሆን የለበ ትም፡፡ የሕዝብ መሰረታዊ መብቶችና የህግ የበላይነትም ሳይሸራረፉ መኖር መከበር አለባቸ ው ማለት ነው፡፡ በህግና በሕዝብ ምርጫ መሰረት፤ሕዝብ ባፀደቀው ህግ መንግስት ስር የሚሰራ ከሆነ ያ መንግስት ከሞላ ጎደል ለብዙሃኑ የሚበጅ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ካልበጀም  ሕዝብ በድምፁ ያውረደዋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ዓይነት ሁኔታ ለመድረስ ገና ብዙ ትግል የሚጠይቀን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ያለውን መንግስት ማንነት አውቆ መገኘት ደግሞ ትግልን ከሚያደናቅፍ ጎጂ ስህተት መቆጠብን ያመጣልና ጠቃሚ ነው፡፡

እስኪ ለማንኛውም  የሰከነ ውይይትን በማድረግ ግንዛቤያችንን ለማዳበር እንጣር፡፡ ታዋቂው ቻይናዊ ያልተመራመረ የመናገር መብት አይኖረውም ያሉት ከበዛብን ቢያንስ ሰሜትን ገርቶ ፤ዕውቀትንና ምርምርን አዳብሮ፤አንቦና አውቆ፤ ከአዋቂዎችም አድምጦ ውይይት ለማድረግ ና ለመማር እንሞክር፡፡